**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በግብርና ቢዝነስ ላይ የተመረኮዘ እድገትን ለማምጣት የሚተጋ ፕሮግራም**

# የመካከለኛ ኢንቬስትሜንት ድጋፍ ፈንድ መመሪያ



**ግንቦት 2010 ዓ.ም**

**የይዘት ማውጫ**


1. መግቢያ ....3
2. የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች....3
3. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት....5
4. የድጋፍ ፕሮጀክት አፈጻጸም....6

4.1. የባንክ ሂሳብ ስለመክፈት....6
4.2. የገንዘብ አለቃቀቅ....6
4.3. የግዥ ስነስርዓት እና የሰነዶች አያያዝ....6
4.4. የሩብ አመት የሂደት ሪፖርቶች....7
4.5. ግምገማ (ክትትል)....7

5. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ....7
6. አባሪዎች....8

አባሪ 1፡- ኮንሰፕት ኖት ማቅረቢያ ቅጽ....8
አባሪ 2; ኮንሰፕት ኖቱን እና ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን መገምገሚያ....10
አባሪ 3፡- ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል....11
አባሪ 4፡- በጀት....13
አባሪ 5፡- የድጋፍ ውል ስምምነት....14
አባሪ 6፡- የሩብ ዓመት የሂደት ሪፖርት እና ማጠናቀቂያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ....18
አባሪ 7፡- ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፤ የፋይናንስ ሪፖርቶች....19
አባሪ 8፡- ገንዘብ እንዲለቀቅ መጠየቂያ ቅጽ....20
አባሪ 9 : የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ፋክት ሽት....21


**አህጽሮተ-ቃላትና ምህጻረ-ቃላት**

የገኢትቢ - ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ
የፕድዩ - የአግሮ ቢግ የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት
የወገኢልጽ - የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት
የወስኮ - የወረዳ ስቲሪንግ ኮሚቴ
የወቴኮ - የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ

## 1. መግቢያ

አግሮ ቢግ በኢትዮጵያ እና በፊላንድ መንግስታት በገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ስር የሚንቀሳቀስ የግብርና ቢዝነስ ልማት ፕሮግራም ሲሆን ፕሮግራሙም
በአማራ ብሔራዊ ክልልዊ መንግስት የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር አስተባባሪ ሆኖ ያስፈጽመዋል፡፡ የአግሮ ቢግ ዓላማ ግብርና መር የኢኮኖሚ እድገት በማምጣት ለድህነት ቅነሳ አስተዋጽኦ ማድረግ ነው፡፡

የአግሮ ቢግ ሁለተኛው ፕሮግራም በሰሜንና በደቡብ አቸፈር፣ በሰሜንና በደቡብ ሜጫ፣ በባህር ዳር ዙሪያ፣ ዴራ ፣ ፎገራና ሊቦከምከም ወረዳዎች የአነስተኛ አርሶ አደሮችን የግብርና ቢዝነስ ለመደገፍ ይሰራል፡፡

## 2. የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ዓላማዎች

የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ዓላማ በእሴት ሰንሰለት ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላት የገንዘብ እና ገንዘብ ነክ አገልግሎቶች አግኝተው ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር እና ተቋማዊ ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡

የድጋፍ ፈንዱ ከአግሮ ቢግ የእሴት ሰንሰለት የተያያዙ መካከለኛ የግብርና ቢዝነስ ኢንቨስትመንቶችን ለመደገፍ ያለመ ሲሆን በዋናነት የሚከተሉትን ዝርዝሮችን የሚከተሉትን ያካተተ ቢሆንም በነዚህ ግን የተወሰነ አይደለም-
የመቀናጀ ድጋፍ ፈንድ ዓላማ የእሴት ሰንሰለቱ ተሳታፊዎች የፋይናንስና የፋይናንስ አገልግሎቶችን በማግኘት ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምሩ እና ኢንተርፕራይዞች ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡ በሚከተሉት ሴክተሮች ላይ ንድፈ ሃሳብ ማቅረብ ይችላል፡

- የጠብታ መስኖን ጨምሮ አነስተኛ የመስኖ ልማት እና የግሪን ሀውስ ቴክኖሎጅ፤
- የግብርና ምርቶችን ማቀነባበሪያ ቁሳቁሶች የሚያሻሽሉ፤
- የአነስተኛ መካናይዜሽን ቁሶችን/ መለዋወጫዎችን እና ጥገናዎችን፣ የትራክተር የመስክ አገልግሎት፣ ቁሳቁሶች ማቀነባበር የመሳሰሉ የግብርና አገልግሎት ማዕከል ግንባታን ጨምሮ የሌሎች ግብዓት አቅርቦት ልማት፤
- አነስተኛ የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንቨስትመንቶች፤
- ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ስምም የሆኑ የአሰራር ዘዴዎች እና የቴክኖሎጅ ፈጠራዎችን ለምሳሌ እንደ ዜሮ ቲሌጅ፣ የሽፋን ሰብሎች፣ ምርትና ሰብል ማፈራረቅ፣ ሀይልን በአግባቡ መጠቀም የተመለከቱ ፈጠራዎች፤
- የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢን የደረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፣ ወይም ሌሎች አስፈላጊ የምስክር ወረቀቶችን በምግብ ነክ ምርቶች፣ በእንሰሳት መኖ እና በሰራተኞች ጤንነት እና የአካባቢ ጥበቃ ረገድ ያሉ የምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፤
  - የጠብታ መስኖና የግሪን ሀውስ ቴክኖሎጅን ጨምሮ አነስተኛ የመስኖ ልማት፤
  - የግብርና ማቀነባበሪያ ቁሳቁሶች እና የመካናይዝድ አገልግሎቶች ሰጭ መሳሪያዎችን፤
  - የግብርና ግብዓቶች አቅርቦት ልማት፣ የግብርና አገልግሎት ማዕከል በማቋቋም አነስተኛ መጠን ያላቸው የመካናይዜሽን ቁሳቁሶችን/ መለዋወጫዎች መሸጫና መጠገኛ፣ የትራክተር የመስክ አገልግሎት፣ ቁሳቁስ ማምረት ወዘተ፤
  - እንደ ዜሮ ቲሌጅ፣ የሽፋን አዝርዕቶች እና ሰብል ማፈራረቅ፣ ሀይልን በቁጠባ መጠቀም ያሉ ከአየር ንብረት ጋር ስምምነት ያላቸው አዲስ አሰራሮች እና ቴክኖሎጅዎች፤
  - አቅርቦት በሚቋረጥባቸው በበጋ ወቅቶች የሚበቅሉ ሰብሎችን ማምረት እና ለገበያ ማቅረብ፤
  - ስልታዊ እና የተቀናጀ የእጽዋት በሽታዎች ቁጥጥር፤

- እንደ ማከማቻ አስተዳደር፣ ማጽዳት፣ ልየታና ደረጃ ማውጣት ያሉ የድህረ ምርት ስብሰባ ተግባራት፤
- በምግብ ምርቶችን ላይ እሴት በመጨመር ማቀነባበር፣ አስተማማኝ የማሽን አጠቃቀም እና ማሽኖችን በሙሉ አቅማቸው መጠቀም፣ ማስተካከል እና መጠገን፤
- የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢን የደረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፣ ወይም ሌሎች አስፈላጊ የምስክር ወረቀቶችን በምግብ ነክ ምርቶች፣ በእንስሳት መኖ እና በሰራተኞች ጤንነት እና የአካባቢ ጥበቃ ረገድ ያሉ የምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፤
- በቢዝነስ አስተዳደር ዘርፍ የክትትል(coaching) አገልግሎት መስጠት፤
- የአቅም ግንባታ ተግባራት ለምሳሌ እንደ ገበያ ጥናት፣ የአመራር ክህሎቶች ወዘተ
- የቢዝነስ ፕላን ለመስራት የወጡ ወጭዎች (ቢበዛ የጠቅላላ በጀቱን 5 በመቶ) ፤
- ለመቀናጀ ድጋፎ ለማግኘት የሚውል የብድር ወለድ፤
- የምርት ማሸጊያዎች ማምረት እና የገበያ ጥናት ስራ፤
- የምግብ ማሰራጫዎችን ለማዘጋጀት እና እንደ አዲስ ለመስራት፤

**2.1 ድጋፎች እና ለድጋፍ የሚያመለክቱ አካላት**

- ለድጋፍ ማመልከት የሚችሉ አካላት፡- አርሶአደሮች፣ የአርሶአደሮች ቡድኖች፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ ኢንተርፕራይዞች እና ስራ ፈጣሪዎች ናቸው፡፡
- ሊሰራ የታቀደው ፕሮጀክት ከአግሮ ቢግ የትኩረት አካባቢ በ100 ኪሎ ሜትር ሬድየስ ውስጥ መሆን ይኖርበታል፡፡
- ለድጋፍ በሚያመለክቱበት ሰዓት ድጋፍ ፈላጊ አመልካቾች በሚመለከተው የአካባቢው ባለስልጣን ዘንድ መመዝገብ ወይም የድጋፍ ውሉን በሚፈራረሙበት ሰዓት መመዝገብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ለአንድ ፕሮጀክት የሚፈቀደው ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ መጠን ብር 1,500,000.00 (50,000 ዩሮ) ይሆናል፡፡
- የሚፈለገው ዝቅተኛው የተዛማጅ ፈንድ መጠን 50 በመቶ፡፡
- ለአንድ አመልካች በአንድ የድጋፍ ጥሪ ከአንድ ጊዜ በላይ ማመልከት አይፈቀድለትም፡፡
- አንድ አመልካች በፕሮግራሙ የቆይታ ጊዜ ውስጥ እንደ ቢዝነሱ ሁኔታ እስከ 3 ጊዜ ድጋፍ ሊገኝ ይችላል፡፡
- ሴት አመልካቾች፣ የሴቶች እና የወጣቶች ቡድን አመልካቾ ችንና የህብረት ስራ ማህበራት ቢያንስ 50 በመቶ አባሎቻቸው ሴቶች ከሆኑ 50 በመቶ የሚሆነውን ተዛማጅ ፈንድ በአይነት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
- ሴት አመልካቾች እና የሴቶች ቡድኖች ተጨማሪ ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡
- የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች የተካተቱባቸው ፕሮፖዛሎች ተጨማሪ ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡
- ከአካባቢ ጥበቃ ዘላቂነትን ከግምት ያስገቡ ፕሮፖዛሎች ተጨማሪ ነጥብ ይሰጣቸዋል፡፡
- ለፕሮጀክቶቹ የሚደረጉ ድጋፎች የሚቆዩበት ከፍተኛ ጊዜ ቢበዛ ውሉ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ እስካሉት ቀጣይ 24 ወራት ነው፡፡
- የቀረበው ፕሮፖዛል መሬት ማግኘትን የሚያካትት ከሆነ ፕሮፖዛሉ በቀረበበት ጊዜ ወይም የድጋፍ ውሉ በተፈረመበት ጊዜ መሬቱ መገኘቱ መረጋገጥ አለበት፡፡
- በፕሮጀክቱ በጀት ላይ የተፈቀዱ ወጭዎች ዝርዝር ተለይቶ መካተት ይኖርበታል፡፡
- ከፕሮጀክቱ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው ወጭዎች እና በድጋፍ በጀት ላይ ያልተገለጹ ወጭዎች ተቀባይነት የላቸውም፡፡

- ለመንግስት ሰራተኛ የሚሰጥ ደመወዝ ተቀባይነት ከሌላቸው ወጭዎች ይመደባል፡፡ ለመንግስት ተቋማት አስተዳደራዊ ወጭዎች እና የመሬት መግዣ ወጭዎችም እንዲሁ ተቀባይነት የላቸውም፡፡

## 3. የማመልከቻ አቀራረብ ሂደት

አመልካቾች ሁለት ደረጃዎች/ሂደቶች አሉት።

የመጀመሪያው አጭር የኮንሰፕት ኖት የሚያቀርቡበትን ሂደት (አባሪ 1ን ይመልከቱ)፡፡

ሁለተኛው ሙሉ ፕሮፖዛል የሚቀርብበት ሂደት ነው (አባሪ 3 ይመልከቱ)

ኮንሰፕት ኖቱና ሙሉው ፕሮፖዛል በእንግሊዝኛ ወይም በአማርኛ ተጽፈው ማቅረብ ይችላሉ፡፡
አመልካቾች ኮንሰፕት ኖቶቱንና የፕሮጀክቶቻቸው ወይም አብዛኛው የፕሮጀክቶቹ ሥራዎች በሚፈጸሙባቸው ወረዳዎች ለሚገኙ የወረዳ ፋይናንስና የኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤቶች መዝገብ ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ አመልካቾች ኮንሰፕት ኖቶቹንና ሙሉ ፕሮፖዛላቸውን ማስረከባቸውን የሚገልጽ ደረሰኝ ከጽ/ቤቶቹ መቀበል አለባቸው፡፡ ሁሉም ኮንሴፕት ኖቶች እና በኋላም የሚቀረቡ ሙሉ ፕሮፖዛሎች በአግባቡ ተመዝግበው ለወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ (የወቴኮ) ይቀርባሉ፡፡

እያንዳንዱ ኮንሴፕት ኖት በአባሪ 2 የሚገኘውን የግምገማ መስፈርት በመጠቀም በሶስት ገምጋሚዎች ይገመገማል፡፡
በቀረቡት ኮንሴፕት ኖት ላይ የመጨረሻ የግምገማ ውጤት ከማሳለፋቸው በፊት የወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላቱ አመልካቾቹ ያሉበትን ሁኔታ በመስክ ምልከታ ሊያረጋግጥ ይችላል፡፡ የዚህ የመስክ ምልከታ አላማ በኮንሰፕት ኖቱ የተካተቱትን መረጃዎች ማረጋገጥ እና የአመልካቾችን አቅም መፈተሽ ነው፡፡

የሶስቱ ገምጋሚዎች ውጤት አማካይ ተሰልቶ ይወሰዳል፡፡ ከዚያም የኮንሰፕት ኖቱ አጠቃላይ ደረጃ ይወጣል፡፡ በዚህም መሰረት የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ውጤቱን አጠናቅሮ ከነምክረ ሀሳቡ ለወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ያስተላልፋል፡፡ የወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ወደ ሙሉ ፕሮፖዛልነት መቀየር ያለባቸውን ኮንሰፕት ኖቶች አጽድቆ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

የተመረጡ ኮንሰፕት ኖቶች ዝርዝር ከነርዕሳቸው፣ ያመልካቾች ስም፣ ቦታዎችና የሚፈልጉት የበጀት መጠን ተካቶባቸው በሚመለከተው የወረዳ ጽ/ቤት ይለጠፋሉ፡፡

አመልካቾች ሙሉውን ፕሮጀክት ፕሮፖዛል አዘጋጅተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል (አባሪ 3 ይመለከቱ)፡፡ አመልካቾች ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎቻቸውን ከዚህ በፊት ኮንሰፕት ኖቶችን ባቀረቡበት የወረዳ ፋይናንስና የኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ያቀርባሉ።

የሙሉ ፕሮፖዛል የግምገማ ሂደቱ ከላይ የኮንሰፕት ኖት ለመገምገም ጥቅም ላይ ከዋለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ በሚገመገምበት ወቅት የግዴታ ከወረዳ ቴክኒክ አባላት መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ሰራተኛ ተወክሎ የመስክ ጉብኝት ማከናወን ይኖርበታል፡፡
ግምገማው ከተጠናቀቀ በኋላ ገምጋሚዎቹ ምክረ ሀሳቦቻቸውን ለወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ ያቀርባሉ፡፡ የግምገማው ውጤት እንደሚከተለው ሊሆን ይችላል፦

ሀ. ኮንሴፕት ኖቱን እንዳለ ማጽደቅ፤
ለ. የፕሮፖዛሉ አዘጋጅ ፕሮፖዛሉን እንዲከልስና መልሶ እንዲያስገባ የሚጠይቅ ወይም

ሐ. ፕሮፖዛሉ ሙሉ ለሙሉ ውድቅ እንዲሆን የሚያደረግ ሊሆን ይችላል፡፡

የወረዳው ስትሪኒግ ኮሚቴ ድጋፍ እንዲደረግላቸው የተመረጡ ፕሮጀክቶችን ምክረ ሃሳብ የማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡

የወረዳው ስትሪንግ ኮሚቴ በምክረ ሃሳብ እንድፀደቁ የሚፈልጋቸውን የፕሮጀክቶችን ዝርዝር ለመጨረሻ ውሳኔ ለአግሮ ቢግ የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት ይልካል። የአግሮ ቢግ የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት የፕሮጀክቱን ዝርዝር  በማየትና ተጨማሪ ግምገማ በማድረግ ከምክረ ሃሳብ ጋር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ  ለመጨረሻ ውሳኔ ይልካሉ፡፡

ፕሮፖዛሎቻቸው ያልተመረጡላቸው አመልካቾች ከነምክንያቱ ያቀረቧቸው ፕሮፖዛሎች እንዳልተመረጡ ይገለጽላቸዋል፡፡ ነገር ግን ኮንሰፕት ኖቶቹ እና ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎቹ ለአመልካቾቹ ተመላሽ አይደረጉም፡፡
የድጋፍ ገንዘብ የተለቀቀላቸው ፕሮጀክቶች ርዕሶች፣ የገንዘብ ተቀባዮች ስሞች፣ ቦታዎቹ፣ የተፈቀዱት በጀቶች እና የድጋፍ ገንዘቡ መጠን በሚመለከተው የወረዳ ጽ/ቤትና በሌሎች የህዝብ ሚዲያ በግልጽ ይለጠፋል፡፡

## 4. የድጋፍ ፕሮጀክት አፈጻጸም

የድጋፍ ውሉ (አባሪ 5) በሚመለከተው የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ እና በአመልካቹ/ድጋፍ ተቀባዩ መካከል ይፈረማል፡፡

### 4.1. የባንክ ሂሳብ ስለመክፈት

የድጋፍ ተቀባዮች በየስማቸው በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም የባንክ ሂሳብ መክፈት ይኖርባቸዋል፡፡ ፕሮጀክቱን የሚመለከቱ ማናቸውም የባንክ እንቅስቃሴዎች በዚህ የባንክ ሂሳብ ይከናወናሉ፡፡
ድጋፍ ጠያቂዎቹ ለፕሮጀክቱ የሚያደርጉት የመከናጀ ፈንድ ተሳትፎ የተፈቀደው የድጋፍ ገንዘብ ወደ ሂሳባቸው ከመተላለፉ በፊት በባንኩ ሂሳብ መግባት ይኖርበታል፡፡

### 4.2. የገንዘብ አለቃቀቅ

የድጋፍ ገንዘብ አለቃቀቁ እንደየፕሮጀክቶቹ ሁኔታ የሚለያይ ሆኖ በድጋፍ ውሉ ላይ በግልጽ መስፈር ይኖርበታል፡፡ የድጋፍ ውሉ መፈረም የቅድሚያ ክፍያ ለአመልካቾች ለመልቀቅ እንደማመልከቻ ይቆጠራል፡፡ ቢበዛ የፕሮጀክቱ 80 በመቶ የሚሆነው ገንዘብ በመጀመሪያ ክፍያ ሊለቀቅ ይችላል፡፡ የድጋፍ በጀት የአለቃቅ ሂደት በኮንትራት ውሉ በግልጽ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

### 4.3. የግዥ ስነስርዓት እና የሰነዶች አያያዝ

ድጋፍ ተቀባዩ ማናቸውንም ግዥዎች የማከናወን ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን የግዥ ሂደቶቹ ተቀባይነት ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ በተቻለ መጠን ድጋፍ ተቀባዩ የሚያከናውናቸውን ግዥዎች ቢያንስ 3 አባላት ባሉበት የግዥ ኮሚቴ ቢከናውን ይመረጣል፡ ከ2500 ብር በላይ የሚያወጣ ግዥ በሚያከናውንበት ጊዜ ቢያንስ ከ3 ቦታዎች የዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡
ድጋፍ ተቀባዩ የተፈቀደለትን የድጋፍ ገንዘብ በአግባቡ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የመጠቀም ኃለፊነት አለበት፡፡
ድጋፍ ተቀባዮች የፕሮጀክቱን ገቢ እና ወጭዎች የሚያሳይ ትክክለኛ የሂሳብ ሰነድ አዘጋጅተው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት የፋይናንስ ሰነዶች የድጋፍ ገንዘቡን ወጭ እና ገቢ ሂሳብ ከነዝርዝር ሰነዶቹ (የባንክ ስተትመንት፣ የግዥ ሰነዶች፣ የዋጋ ማቅረቢያዎች (ፕሮፎርማዎች)፣ የግዥ ኮሚቴ ቃለጉባኤዎች፣ ደረሰኞች እና ኢንቮይሶች) መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርቡት የሂሳብ ሰነዶች የፕሮጀክቱን የገንዘብ እንቅስቃሴ ከሌሎች ገቢዎች ለይተው ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 4.4. የሩብ አመት የሂደት ሪፖርቶች

ድጋፍ ተቀባዮች በየሩብ አመቱ ለወረዳ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ቢሮ የሂደት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል (አባሪ 6)፡፡ የወረዳ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሪፖርቱን ለአግሮ ቢግ ፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት ይልካሉ። ተጠቃሚዎች እያንዳንዱ ሪፖርት ማድረጊያ ወቅት እንዳበቃ የፕሮጀክቱን ገቢ እና ወጭ መግለጫ ሪፖርት ያቀርባሉ (አባሪ 7)፡፡ ይህ የፋይናንስ ሪፖርት ከሂደት ሪፖርቱ ጋር ተያይዞ ይቀርባል፡፡

### 4.5. ግምገማ (ክትትል)

አግሮ ቢግ የድጋፍ ፕሮጀክቶቹን በየጊዜው ይከታተላል (ይገመግማል)፡፡ ግምገማውን ሲያከናውንም፡-

- የፕሮጀክቱን ገንዘብ በትክክል ስራ ላይ እንዳዋለ እና የሂሳብ አያያዙ እንዴት እንደሆነ እንዲሁም ጥቅም ላይ ያዋለው ገንዘብ በሰነድ ተደግፎ መቅረብ አለመቅረቡን ይመለከታል፤
- የፕሮጀክቱን ቴክኒካዊ አፈጻጸም ተመልክቶ አፈጻጸሙ ፕሮጀክቱ በተያዘለት የሂደት ግብ (ማይል ስቶን) መሰረት እየሄደ መሆን አለመሆኑን ይፈትሻል፡፡

## 5. የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ

የድጋፍ ተጠቃሚው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ያቀርባል (አባሪ 6)፡፡ የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርቱ በሂደት ሪፖርቱ የተጠቀሱ ነጥቦችን አጠቃሎ ከማቅረብ ባሻገር ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ ያስገኛቸውን ውጤቶች ያካትታል፡፡

### 5.1 የፕሮጀክቱን ፋይል መዝጋት

የአግሮ ቢግ የገጠር ፋይናንስ አማካሪና የወረዳው ቴክኒክ ኮሚቴ በጋራ የፕሮጀክቱን ፋይል እንዲዘጋ የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህን ሲያደርጉ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ ሂደቶች ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል፡-

- የፕሮጀክቱን የፋይናንስ ሂሳብ መዝጋትና ተመላሽ ገንዘቦች ሁሉ በትክክል መግባታቸውን እንዲሁም ክፍያዎች ተጠናቅቀው መፈጸማቸውን ማረጋገጥ፤
- የድጋፍ ተቀባዩ ያቀረበውን የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ማጽደቅ፤
- ወረዳው የፕሮጀክቱን የመጨረሻ ኦዲት በወረዳው የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ኦዲተሮች እንዲያስገመግም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- የድጋፍ አመልካቹ ግዴታዎችን በአግባቡ እንደተወጣ በማረጋገጥ አመልካቹ የድጋፍ መዝጊያ ደብዳቤ አዘጋጅቶ መስጠት፡፡ ከዚህ በኋላ ድጋፍ ተቀባዩ ሁሉንም የፕሮጀክት ሰነዶች እና የሂሳብ መዛግብት መንግስት ለኦዲት በሚፈልግበት ጊዜ ለማቅረብ እንዲችል ለ3 ዓመታት ተይዘው እንዲቆዩ ማሳሰብ፤
- ቀሪው 20 በመቶ የፕሮጀክት ድጋፍ ገንዘብ ለድጋፍ ጠያቂው እንዲለቀቅለት ማድረግ፤
- የፕሮጀክት ፋይል ለመዝጋት የሚደረግ የመጨረሻ ውሳኔ የሚተላለፈው በፕሮጀክት ድጋፍ ዩኒቱ ይሆናል፡፡

ፕሮጀክቱ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ ለፕሮጀክቱ የተለቀቀው የድጋፍ ገንዘብ የመጨረሻ ኦዲት ይከናወናል፡፡ በዚህም ወረዳው እና የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኦዲተሮች እያንዳንዱን የድጋፍ ፕሮጀክቶቹን የሂሳብ መዛግብት እና ወጭዎች ኦዲት ያደርጋሉ፡፡

## 6. አባሪዎች

**አባሪ 1:- ኮንሰፕት ኖት ማቅረቢያ ቅጽ**

**የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ**

**ኮንሰፕት ኖት**

| **የፋይል ቁጥር** | |
|---|---|

(ለጽ/ቤት አገልግሎት ብቻ የሚውል)

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ:- | |
| የአመልካቹ ስም:- | |
| ህጋዊነት: | |

| የአመልካቹ ዝርዝር አድራሻ እና የፕሮጀክቱ ዓላማ:- | |
|---|---|
| የተመዘገበ የፖስታ አድራሻ:- | |
| የስልክ ቁጥር:- | |
| የፕሮጀክቱ ወኪል:- | |
| የወኪሉ የኢሜል እና ስልክ | |
| አድራሻ:- | |

ኮንሰፕት ኖት ለማዘጋጀት የሚጠቅም መመሪያ

የሚከተለውን ሰንጠረዥ ከሁለት ገጽ ባልበለጠ እንዲሞሉ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ፡ | |
| ፕሮጀክቱ የሚገኝበት ቦታ (ቦታዎች)፡-<br>ፕሮጀክቱ በየትኛው ወረዳ እና ቀበሌ እንደሚከናወን ይጠቅሱ | |
| የፕሮጀክቱ አጠቃላይ የቆይታ ጊዜ (ወራት)፡- | |
| የተጠየቀው የድጋፍ ገንዘብ መጠን (በብር) | ብር |
| የድጋፍ ጠያቂው ከራሱ የሚያቀርበው የተዛማጅ ፈንድ ድርሻ | በመቶኛ እና በአሃዝ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | ፕሮጀክቱን በመተግበር ሊለውጧቸው ያሰቧቸው ነገሮች ምን ምንድን ናቸው?<br>ከፕሮጀክቱ በበለጠ የሚጠቀመው ማን ነው? የተባሉት ሰዎች እንደተጠቀሙ በምን ማሳየት ይቻላል?<br>ከፕሮጀክቱ የሚጠቀሙ ሌሎች ሰዎች ይኖሩ ይሆን? የተባሉት ሰዎች እንደተጠቀሙ በምን ማሳየት ይቻላል? |
| የመጨረሻ ተጠቃሚዎች (እነኝህ አካለት በዕቅዱ እንዴት ተሳታፊ ነበሩ) | ተጠቃሚዎች እንዴት እንደተሳተፉ እንዲገልጹ ይጠየቃል፡፡ |
| የሚገኙ ውጤቶች | |
| ዋና ዋና ተግባራት | |
| ሌሎች መረጃዎች<br>በዚህ ፕሮጀክት ሴቶች የሚኖራቸው ድርሻ ምን ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚጠቀሙ በዝርዝር ይግለጹ፡፡<br>ፕሮጀክቱ ተፈጻሚ ሲሆን ሊሰሩ የታሰቡ የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ካሉ ይጠቀሱ፡፡ | |

ስም፣ቀን እና የአመልካች ፊርማ፡-

**አባሪ 2; ኮንሰፕት ኖቱን እና ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን መገምገሚያ**

የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ

| | |
|---|---|
| **ቅጹን የሞላው፡-** | |
| **የፕሮፖዛሉ ቁጥር፡-** | |
| **የአመልካቹ ስም፡-** | |
| **የፕሮጀክቱ ርዕስ፡-** | |

**የውጤት አሞላል መመሪያ**

0 = ያልቀረበ ወይም በጣም ደካማ፣ 20= እጅግ በጣም ጥሩ

**የመገምገሚያ ቅጽ፡-** የኮንሰፕት ኖት እና ሙሉ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ውጤት መስጫ መስፈርት

| **መስፈርት** | **ከፍተኛ ውጤት** | **የገምጋሚው ውጤት** |
|---|---|---|
| የእሴት ሰንሰለት የሚያጠናክር/ዕገዛ  የሚያደርግ መሆኑ | 20 | |
| የፕሮፖዛሉ ኮንሰፕት/ፅንሰ ሀሳብ ችግር ፈች መሆኑ | 20 | |
| የሚጠበቅው ውጤት መገለፅ መቻሉ | 20 | |
| የአመልካቹ ከዚህ በፊት ያለው ልምድ | 20 | |
| **ድንበር ተሻጋሪ ጉዳዮች ማቀፍ፡-** | | |
| ሴት አመልካቾች ወይም የሴት አመልካቾች ቡድን | 10 | |
| የአካል ጉዳት ያለባቸውን ሰዎች ያሳተፈ ወይም ተጠቃሚ ማድረጉ | 5 | |
| የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን ከግምት ያስገባ መሆኑ | 5 | |
| **ድምር** | **100** | |

**አባሪ 3፡- ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል**

**የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ**

**ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል**

| | |
|---|---|
| **የፋይል ቁጥር** | |

(ለጽ/ቤት አገልግሎት ብቻ የሚውል)

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ርዕስ፡- | |
| የአመልካቹ ስም፡- | |
| በይፋ የተመዘገበ አድራሻ፡- | |
| የምዝገባ ቁጥር (ወይም ይህን የሚተካ አቻ)፡- | |
| የህጋዊነት ደረጃ፡- | |
| የአመልካች/ወኪል፡- | |
| የስልክ ቁጥር፡- | |
| የኢሜል አድራሻ፡- | |
| ድረገጽ፡- | |

አባሪ፡- እባክዎን የሚከተሉትን ሰነዶች እንደአስፈላጊነቱ ያያይዙ

1. የንግድ ፈቃድ እና ምዝገባ የምስክር ወረቀት
2. የመመስረቻ ጽሁፍ
3. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር
4. ሌሎች

**ፕሮጀክቱ**
ፕሮጀክቱ የሚቆይበት ጊዜ ---- ወራት ነው፡፡

**የፕሮጀክቱ መግለጫ (ቢበዛ 1ገጽ)**

- የሚጠበቁ ውጤቶችን ይግለጹ፤ ይህን ሲያደርጉ ፕሮጀክቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎችን የአኗኗር ሁኔታ እንዴት ሊቀይር እንደሚችል ያመልክቱ፡፡
- እያንዳንዱ ተግባር/የስራ ዝርዝር እንዴት ውጤት እንደሚያመጣ እና ተግባሩ በምን ምክንያት እንደተመረጠ ያብራሩ፡ ፡
- በኮንሰፕት ኖቱ የተካተቱ ሁኔታዎች በጊዜ ሂደት እንዴት ሊቀየሩ እንደሚችሉ ይግለጹ /ያመልክቱ፡፡

**ስነዘዴ (አሰራር ዘይቤ) (ቢበዛ 1 ገጽ)**

- ሊተገብሩ ያሰቡትን የአሰራር ዘዴው የተመረጠበትን ምክንያት ይግለጹ፡፡
- ፕሮጀክቱ የሚያመጣቸውን ተጽዕኖዎች ከተቻለ በአሀዝ እና በመረጃ አስገድፈው በቴክኒክ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ደረጃዎች ያሉ ተጽዕኖዎችን ይግለጹ፡፡

**የተፈለገው የድጋፍ ፈንድ መጠን**
የተጠየቀው የድጋፍ ፈንድ መጠን በብር
ከአመልካቹ የሚቀርብ አስተዋጽኦ (ቢያንስ የፕሮጀክቱን 50 በመቶ) በብር
ሴቶች እና የሴቶች ቡድን አባላት የራሳቸውን አስተዋጽኦ በአይነት የሚያቀርቡ ከሆነ ዝርዝሩና መጠኑ

**የአመልካቹ ልምድ (ቢበዛ 1 ገጽ)**
ይህ መረጃ ድጋፍ ከጠየቁበት ፕሮጀክት ጋር በተያያዘ አመልካቹ ያለውን ተጨባጭ የስራ ልምድ እና ፕሮጀክቶችን የመምራት ልምድ የሚገመገምበት ነው፡፡

**የአመልካቹ መግለጫ**
ፊርማው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተው አመልካች እንዲሁም የአመልካቾች ህጋዊ ፈራሚ የሚከተለውን መግለጫ ሰጥቷል፡-

- አመልካቹ የቀረበውን ፕሮጀክት ለመተግበር የሚያስችል የገንዘብ ምንጭ፣ ሞያዊ ክህሎት እና ብቃት አለው፤
- አመልካቹ ፕሮጀክቱን ከማዘጋጀት፣ ከመምራት እና ከመፈጸም ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ሃላፊነት አለበት፤ ይህን ተግባር በተመለከተም እንደዋና ባለቤት እንጅ እንደ ሶስተኛ ወገን አገናኝ ሆኖ ላለማገልገል ቃል ገብቷል፤
- አመልካቹ በተጠየቀ ጊዜ ከፕሮጀክቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማናቸውንም በመመሪያው ላይ የተጠቀሱ ሰነዶች ያቀርባል፤
- የድጋፍ ገንዘቡ ከተፈቀደለት አመልካቹ በመመሪያው አባሪ የተደረገውን መደበኛ የድጋፍ ውል ስምምነት ተቀብሎ የውሉ ሁኔታዎች ሊያሟላ ተስማምቷል፡፡

**በአመልካቹ ወገን የቀረበ ፈራሚ**

| | |
|---|---|
| ስም ፡- | |
| ፊርማ፡- | |
| ሃላፊነት፡- | |
| ቀን፡- | |

**አባሪ 4፡- በጀት**

**የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ**

| **የፕሮጀክቱ ዝርዝር ጉዳዮች፣ የሚፈልጉት በጀት እና የበጀት ርዕስ** | **መለኪያ** | **ዋጋ/መለኪያ** | **ጠቅላላ ዋጋ** | **ማብራሪያ** |
|---|---|---|---|---|
| 1. (የበጀት ይዘቱ ስያሜ/ኮምፓኔንት) | | | | |
| 1.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| 1.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር 1** | | | | |
| 2. (የበጀት ይዘቱ ስያሜ/ኮምፓኔንት) | | | | |
| 2.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| 2.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| 2.3. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር 2** | | | | |
| 3. (የበጀት ይዘቱ ስያሜኮምፓኔንት) | | | | |
| 3.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| 3.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| 3.3. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | |
| **ንዑስ ድምር 3** | | | | |
| **አጠቃላይ ድምር** | | | | |

**አባሪ 5፡- የድጋፍ ውል ስምምነት**

የመካለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈነድ

**የድጋፍ ውል ስምምነት**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኢትዮጵያ-ፊንላንድ የግብርና ቢዝነስ ተኮር ልማት

(የድጋፍ ውል ስምምነት መለያ ቁጥር ወረዳ ኤምኢ 2018----)

("ውሉ" ተብሎ የሚጠቀሰው)

የወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት (የወገኢልጽ)

አድራሻ፡-

ወኪል (ኮንታክት ፐርሰን)፡-

የስልክ ቁጥር፡-

ኢሜል አድራሻ፡-

የፖስታ አድራሻ፡- ፖ.ሳ.ቁ.

የመኀብኛ አድራሻ፡-

በአንድ ወገን የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት

እና

ወኪል (ኮንታክት ፐርሰን)፡-

የፓስፖርት ወይም የመታወቂያ ቁጥር፡-

የስልክ ቁጥር፡-

ኢሜል አድራሻ፡-

የፖስታ አድራሻ፡-

የመኀብኛ አድራሻ፡-

በሌላ ወገን ዋሱን ወክሎ ግራ ቀኙ እንደሚከተለው ተስማምተዋል፤

**የውሉ ልዩ ሁኔታዎች**

**አንቀጽ 1፡- ዓላማ**

1.1. የዚህ ውል አላማ የወረዳው የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ‹የፕሮጀክቱ ስም ይሞላ› የሚባለውን ፕሮጀክት በገንዘብ ለመደገፍ ነው፡፡

1.2. ድጋፍ ጠያቂው በዚህ ውል እና ውሉ አባሪ አድርጎ በያዛቸው ሌሎች ሰነዶች ድንጋጌዎች እና ሁኔታዎች መሰረት የተጠቀሰው የድጋፍ ገንዘብ ይለቀቅለታል፡፡

1.3. የድጋፍ ውል ተቀባዩ የድጋፍ ገንዘቡን ተቀብሎ ፕሮጀክቱን ለመፈጸም ሃላፊነት ወስዷል፡፡

**አንቀጽ 2፡- የፕሮጀክቱ የመፈጸሚያ ጊዜ**

2.1. ይህ ውል ሁለቱ ተፈራራሚ አካላት ከፈረሙበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ውሉ ከመፈረሙ በፊት የወጡ ወጭዎች በውሉ መሰረት እንዲተኩ ሊጠየቅ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ (ይህ ግን በበጀቱ ላይ የተመለከቱ የቢዝነስ ልማት ማሳለጫ ዋጋዎችን/ ወጭዎችን አያካትትም)፡፡

2.2. ይህ ፕሮጀክት መፈጸም የሚጀምረው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች ከተፈራረሙበት ሰዓት ጀምሮ ነው፡፡

2.3. የፕሮጀክቱ መፈጸሚያ ጊዜ ‹ወራቱ ይጻፉ› ነው፡፡

2.4. የዚህ ውል መፈጸሚያ ጊዜ ሊራዘም የሚችለው የድጋፍ ውል ተቀባዩ እና የወረዳው ገንዘብ እና ልማት ጽ/ቤት በሚያደርጉት የጋራ የጽሁፍ ስምምነት መሰረት ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 3፡- ፕሮጀክቱን በገንዘብ ስለመደገፍ**

3.1. የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ለፕሮጀክቱ ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ› ፈቅዷል፡፡

3.2. ቢበዛ የፕሮጀክቱን ጠቅላላ ዋጋ 80 በመቶ የሚሆነው የድጋፍ ገንዘብ በመጀመሪያ ዙር ክፍያ መልክ የሚለቀቅ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ከተፈለገ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የሚለቀቅ ይሆናል፡፡

3.3. ድጋፍ ተቀባዩ የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ዋጋ 50 በመቶ ማለትም ብር ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ› ከራሱ አስተዋጽዖ ለማድረግ ተስማምቷል፡፡

3.4. ብር ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ› ግምት ያለው አስተዋጽዖ በዓይነት እንዲደረግ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ የድጋፉ የመጨረሻ አስተዋጽዖ የሚወሰነው የማጠናቀቂያው ሪፖርት እና የተጠናቀቀው የሂሳብ ሪፖርት ቀርቦ በወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሲጸድቅ በሚታየው ሂሳብ መጠን ሆኖ በአግሮ ቢግ ፕሮግራም ዩኒት ስምምነት ሲደረስ ነው፡፡

**4. ሪፖርት እና የክፍያ አፈጻጸም**

4.1. የቅድመ ክፍያ ገንዘብ ቀጥሎ በተዘረዘረው መንገድ ይፈጸማል፡፡ የመጀመሪያ ቅድሚያ ክፍያ ውሉ በተፈረመ እና ተዛማጅ ፈንዱ በድጋፍ ጠያቂው የባንክ ሂሳብ ውስጥ መግባቱ በተረጋገጠ በ30 ቀናት ውስጥ ይለቀቃል፡፡

1ኛ የቅድሚያ ክፍያ ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ›

2ኛ ቅድሚያ ክፍያ ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ›

3ኛ ቅድሚያ ክፍያ ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ›

አጠቃላይ የቅድሚያ ክፍያ ድምር፡- ‹የገንዘቡ መጠን ይጠቀስ› በአንቀጽ 3.1 እንደተመለከተው ከፍተኛው የሚለቀቅ ቅደሚያ ክፍያ የፕሮጀክቱን ዋጋ 80 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

4.2. የመጨረሻው ክፍያ የአጠቃላይ የፕሮጀክቱን ዋጋ 20% በመቶ ሲሆን ይህም የሚለቀቀው 3.4 የተጠቀሱት ሲሟሉና የመጨረሻ የሂሳብ ሰነዶች ቀርበው ሲጸድቁ ነው፡፡

4.4. የባንክ ሂሳብ ዝርዝር መረጃዎች፡-

- የባንኩ ስም እና የባንኩ ቅርንጫፍ ስም፡-
- የባንኩ አድራሻ፡-
- የሂሳቡ ስም፡-
- የሂሳብ ቁጥር፡-

**አንቀጽ 5፡- አድራሻ**

5.1 ከዚህ ውል ስምምነት ጋር ተያያዥነት ያለው ማንኛውም ግንኙነት በጽሁፍ መከናወን ያለበት ሲሆን ሰነዱ የፕሮጀክቱን ቁጥር እና ርዕስ እንዲይዝ ሆኖ በተቀባዩ በተመዘገበው አድራሻው ይላክለታል፡፡

‹ተገቢውን አድራሻ እዚህ ላይ ይጻፉ›

**አንቀጽ 6፡- ሌሎች ጉዳዮች**

6.1. የሂደት ሪፖርት፣ግምገማና የግምገማ ውጤቶችን ማሳወቅ፡- ድጋፍ ጠያቂው በፕሮጀክቱ ቆይታ በየሩብ አመቱ የሂደት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ድጋፍ ጠያቂው የመንግስት አካላት ወይም የረጅ ድርጅቱ ወኪል በፕሮጀክቱ ሳይት በመገኘት የቅኝት ጥናት ለማከናወን ወይም በአግሮ ቢግ የሚዘጋጁ የፕሮሞሽን ቁሶችን ለማዘጋጀት የሚውል ግብዓት ከፕሮጀክቱ ለመውሰድ በሚመጡበት ጊዜ ወይም የፕሮጀክቱን ውጤቶች ለማሰራጨት ፈልጎ መረጃ በሚጠይቅበት ጊዜ አስፈላጊውን ሁሉ ትብብር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6.2. ፕሮጀክቱን ስለመዝጋት፡- ፕሮጀክቱ በሚጠናቀቅበት ጊዜ ድጋፍ ጠያቂው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ድጋፍ ተቀባዩ ያሉበትን የውል ግዴታዎች በሙሉ በአግባቡ መወጣቱን አረጋግጦ የመዝጊያ ደብዳቤ እስከሚሰጥበት ሰዓት ድረስ ማንኛውም የድጋፍ ውል ስምምነት ግዴታዎች በድጋፍ ተቀባዩ ላይ ጸንተው ይቆያሉ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ቀሪው 20 በመቶ ለመጨረሻ ክፍያ ይለቀቃል፡፡ ከዚህ ላይ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት በድጋፍ መልክ የሚፈቀደው የፕሮጀክት ገንዘብ ከፕሮጀክቱ ጠቅላላ ወጭ 50 በመቶ መብለጥ እንደማይኖርበት ነው።

6.3. ድጋፍ ተቀባዩ የተለቀቀለት ገንዘብ በውል ስምምነት ለተገባበት ተግባር ብቻ ማዋሉን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ውጭ የሚደረግ የበጀት ሽግሽግም ይሁን በአንድ የበጀት ርዕስ ላይ ሊውል የታሰበ ተጨማሪ በጀት ካስፈለገ ጉዳዩ በቅድሚያ በወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በጽሁፍ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባዋል፡፡

6.4. የፕሮጀክት ሂሳቦችን እና ሰነዶችን መመርመር፡- እንደአስፈላጊነቱ አግሮ ቢግ ለማንኛውም ጊዜ የፕሮጀክቱን ውጤቶች እና የሂሳብ ሰነዶች እንዲመረመሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡ የድጋፍ ተቀባዩ በማንኛውም ሰዓት ሪፖርቶች፣ ሰነዶች እና የሂሳብ መዛግብት እንዲመረመሩ ያለምንም ማመንታት መፍቀፍ ይኖርበታል፡፡

6.5. የድጋፍ ፕሮጀክቱን ኦዶት ማስደረግ ወይም ማስመርመር፡- የፕሮጀክቱ ተግባራት እና ሂሳቦች ከመንግስት ሃላፊነት በተሰጠው አካል ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች ይመረመራሉ፡፡ በመሆኑም በፕሮጀክቱ አገልግሎት የዋሉ ማናቸውም ገንዘብ ነክ ሰነዶች እና የግዥ ሰነዶች ለቀጣይ 3 ዓመት በጥንቃቄ ተሰንደው የሚመለከተው የመንግስት አካል ወይም ኦዲተር ለምርመራ ሲጠይቅ መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

6.6. ጉዳት እና ካሳ፡- ድጋፍ ጠያቂው ስምምነት የተደረገበትን ፕሮጀክት በራሱ የማስኬድ፣ የመፈጸም እና የማንቀሳቀስ ሙሉ መብት አለው፡፡ በመሆኑም በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ላይ ለተከሰቱ ጉዳቶች የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ፣ የወረዳ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት እና አግሮ ቢግ ምንም አይነት ሃላፊነት አይወስዱም፡፡

6.7. የግጭት አወጋገድ፡- በዚህ ውል ስምምነት ላይ ያለመግባባት ከተከሰተ ድጋፍ ተቀባዩ እና የወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በጋራ ጉዳዩን በድርድር ለመፍታት ተስማምተዋል፡፡ ሆኖም ግን በጉዳዩ ላይ መግባባት ካልቻሉ ችግሩ ለክልሉ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ቢሮ ተላልፎ በመንግስት ድርድር አሰራር ሂደት እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 7፡- አባሪዎች**

7.1. የሚከተሉት ሰነዶች ከውል ስምምነት ሰነዱ ጋር አባሪ ተደርገው  የውል ስምምነቱ የማይነጣጠል አካል ሆነው ይቆጠራሉ፡-

አባሪ 1፡- የፕሮጀክቱ መግለጫ (ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እና ኮንሰፕት ኖት)

አባሪ 2፡- የፕሮጀክቱ በጀት

አባሪ 3፡- በድጋፍ ተቀባዩ ተፈጻሚ የሚሆን የግዥ መመሪያ

7.2. በዚህ የውል ስምምነት ድንጋጌዎች እና አባሪ በተደረጉት ሰነዶች መካከል ግጭት ከተከሰተ ለውሉ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

ይህ ውል ስምምነት በአማርኛ ወይም እንግለዝኛ ቋንቋ በ3 ኦሪጅናል ኮፒዎች ተዘጋጅቶ  1ኛው ኦሪጅናል ኮፒ ለድጋፍ ተቀባዩ፣ 1ኛው ኦሪጅናል ኮፒ ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት 1ኛው ኦሪጅናል ኮፒ ደግሞ ለአግሮ ቢግ የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒት ተሰቷል፡፡

**በድጋፍ ፈላጊው ወገን፡-**

ስም፡-

ኃላፊነት፡-

ፊርማ፡-

ቀን፡-

**በወረዳው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ወገን፡-**

ስም፡-

ኃላፊነት፡-

ፊርማ፡-

ቀን፡-

**አባሪ 6፡- የሩብ ዓመት የሂደት ሪፖርት እና ማጠናቀቂያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ**

የመካከለኛ ኢንቨስትሜንት ድጋፍ ፈንድ

የሪፖርቱ ወቅት፡-

የፕሮጀክቱ ቁጥርና ርዕስ፡-

የድጋፍ ተቀባዩ/ የፕሮጀክት ፈጻሚ ድርጅቱ ስም፡-

ወኪል/ ኮንታክት ፐርሰን፡-

**<u>የሪፖርቱ ቢጋር</u>**

1. የሂደት ሪፖርት
    - ግብዓቶች፡- ሥራ ላይ የዋሉ ዕቃዎች/ ሀብቶች
    - ተግባራት፡- የተሳታፊዎች ብዛት (ወንድ/ ሴት)
    - ተግባራት፡- እንደዕቅዱ የተጠናቀቁ
    - ተግባራት፡- በዕቅዱ ልክ ያልተጠናቀቁ
    - ውጤቶች፡- በእቅዱ መሰረት የተገኙ ውጤቶች እና ታቅደው ያልተሳኩ

2. የውጤት ግምገማ
    - ፕሮጀክቱ በዚህ ወቅት ሊያከናውነው ያቀደው ዋና ግብ ምን ነበር?
    - ግቡ ተሳካ ወይስ አልተሳካም? ለስኬቱ ወይም ላለመሳካቱ ዋና ምክንያት ምንድን ነበር?
    - አፈጻጸሙ በእቅድ መሰረት እየሄደ ነው? ካልሆነስ ምን ዓይነት ማስተካከያ እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ?
    - በቀጣዩ ጊዜ ሊከናወን የሚጠበቁ ዋና ዋና ስኬቶች ምን ምንድን ናቸው?

**አባሪ 7፡- ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ፤ የፋይናንስ ሪፖርቶች**

**የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ**

የፕሮጀክቱ ቁጥርና ስም፡- የሪፖርት ጊዜ፡-

የድጋፍ ተቀባዩ/ የፕሮጀክት ፈጻሚው ድርጅት ስም፡- የወኪሉ ስም

| **የፕሮጀክቱ ዝርዝር ጉዳዮች፣ የሚፈልጉት በጀት እና የበጀት ርዕስ** | | **በጀት በበጀት ርዕስ** | **የባለፈው ሪፖርት ወቅት ድምር** | **የባለፈው ሪፖርት ወቅት ወጭዎች** | **አጠቃላይ ወጭዎች** | **አሁን ያለው ቀሪ ሂሳብ** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **የቅድሚያ ክፍያ ግራንት** | | | | | | |
| 1. (የበጀት ይዘቱ ስያሜ/ኮምፓኔንት | | | | | | |
| 1.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| 1.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| **የበጀት ይዘት 1 ንዑስ ድምር** | | | | | | |
| 2. (የበጀት ይዘቱ ስያሜ)/ኮምፓኔንት | | | | | | |
| 2.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| 2.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| 2.3. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| **የበጀት ይዘት 2 ንዑስ ድምር** | | | | | | |
| 3. (የበጀት ይዘቱ ስያሜ)/ኮምፓኔንት | | | | | | |
| 3.1. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| 3.2. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| 3.3. (የበጀት ርዕሱ ስም) | | | | | | |
| **የበጀት ይዘት 3 ንዑስ ድምር** | | | | | | |
| **አጠቃላይ ድምር** | | | | | | |

**አባሪ 8፡- ገንዘብ እንዲለቀቅ መጠየቂያ ቅጽ**

የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ

**የገንዘብ መጠየቂያ ቅጽ** የቅድሚያ ክፍያና የመጨረሻ ክፍያ

ቀን፡-

የሪፖርቱ ጊዜ፡-

የፕሮጀክቱ ቁጥርና ርዕስ፡-

የድጋፍ ተቀባዩ/ የፈጻሚ ድርጊቱ/ ወኪሉ ስም፡-

| | | |
|---|---|---|
| የፕሮጀክት አጠቃላይ በጀት | ብር | |
| በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ተቀባዩ የተላለፈ ገንዘብ | ያነሰ | |
| በፋይናንስ ስርዓቱ መሰረት የተጠየቀ የቅድሚያ ክፍያ መጠን ወይም | ያነሰ | |
| ቀሪ ድጋፍ | ድምር | |

| **የቅድሚያ ክፍያ መጠየቂያ ቼክ ሊስት** | **አዎ** | **የለም** |
|---|---|---|
| የሩብ አመት ሪፖርት ገቢ ተደርጓል | | |
| ፋይናንሻል ሪፖርት ገቢ ተደርጓል | | |
| የግምገማ ጉብኝት ተከናውኗል | | |
| | | |
| **የመጨረሻ ክፍያ ቼክ ሊስት** | **አዎ** | **የለም** |
| የማጠናቀቂያ ሪፖርት አባሪ ተደርጓል | | |
| የመጨረሻ የፋይናንስ ሪፖርት አባሪ ተደርጓል | | |
| የኦዲት ሪፖርት አባሪ ተደርጓል | | |
| የባንክ ሂሳብ ባላንስ + የጥሬ ገንዘብ ባላንስ ድጋፍ ተቀባዩ በእጁ ከያዘው ገንዘብ መጠን ጋር ይጣጣማል | | |
| ቢያንስ የጠቅላላ ፕሮጀክቱን 50 በመቶ ተዛማጅ ፈንድ ቀርቧል | | |
| ከላይ ያለው የገንዘብ መልቀቂያ መጠየቂያ ተረጋግጦ ድምሩ ትክክል ነው | | |

ፊርማ፡-

የድጋፍ ጠያቂው ህጋዊ ወኪል ስም፡-

## አባሪ 9 : የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ፋክት ሽት

| | የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ |
|---|---|
| ፈጻሚ አጋር | የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም |
| የአግሮ ቢግ የሚሰራባቸው ወረዳዎች | በሰሜንና ደቡብ አቸፈር፣ ሰሜንና ደቡብ ሜጫ፣ ባህር ዳር ዙሪያ፣ ዴራ፣ ፎገራ፣ እና ሊቦ ከምከም ወረዳዎች ናቸው |
| የአግሮ ቢግ የድጋፍ የእሴት ሰንሰለቶች | ሽንኩርት፣ ድንች፣ ሩዝ፣ በቆሎ፣ ቲማቲም፤ ወተት ሀብት፤ በግና ፍየል ማድለብ ፤ ዶሮ እርባታ ፕሮግራሙ ለድጋፍ አስጣጡ የሚመጥኑ ሌሎች የእሴት ሰንሰለቶችን ሊያካትት ይችላል |
| ተጠቃሚ መሆን የሚችሉ አመልካቾች | አርሶአደሮች፣ የአርሶአደሮች ቡድኖች፣ የህብረት ስራ ማህበራት፣ ኢንተርፕራይዞች፣ ስራ ፈጣሪዎች እና ማህበራዊ ተቋማት ናቸው፡፡ |
| ዓላማ | የመካከለኛ ኢንቨስትመንት ድጋፍ ፈንድ ዓላማ የእሴት ሰንሰለቱ ተሳታፊዎች ገንዘብ እና የገንዘብ አገልግሎቶችን በማግኘት ተወዳዳሪነታቸውን እንዲጨምሩ እና ኢንተርፕራይዞች ዘላቂነታቸው እንዲረጋገጥ ማድረግ ነው፡፡<br><br>የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በአግሮ ቢግ የእሴት ሰንሰለቶች ማዕቀፍ ውስጥ የሚያርፉ መካከለኛ የግብርና ቢዝነስ ኢንቨስትመንቶችን የሚመለከት ሲሆን ዝርዝሩ ሌሎችንም የሚጨምር ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፡-<br>• የጠብታ መስኖን ጨምሮ አነስተኛ የመስኖ ልማት እና የግሪን ሀውስ ቴክኖሎጅ፤<br>• የግብርና ማቀነባበሪያ ቁሳቁሶች እና መካናይዝድ የመስክ አገልግሎቶች፤<br>• የግብርና ግብዓት አቅርቦትን የሚያሻሽሉ ማልትም መካናይዜሽን ቁሶችን/ መለዋወጫዎችን እና ጥገናዎችን፣ የትራክተር የመስክ አገልግሎት፣ ቁሳቁሶች ማቀነባበር የመሳሰሉ የግብርና አገልግሎት ማዕከል ግንባታን ብመገንባት የግብዓት አቅርቦት ልማት ማሻሻል፤<br>• ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥ ያላቸው የአሰራር ዘዴዎች እና የቴክኖሎጅ ፈጠራዎችን ለምሳሌ እንደ ዜሮ ቲሌጅ፣ የሽፋን ሰብሎች፣ ሰብል ማፈራረቅ፣ ሀይልን በአግባቡ መጠቀም የመሳሰሉትን የፈጠራዎች ስራዎች የሚያበረታቱ፤<br>• አቅርቦት በሚቋረጥባቸው ደረቃማ ወቅቶች የሚበቅሉ ሰብሎችን ማምረት እና ለገበያ ማቅረብ፤<br>• ስልታዊ እና የተቀናጀ የእጽዋት በሽታዎች ቁጥጥር፤<br>• የድህረ ምርት አያያዝ ለምሳሌ የማከማቻ/መጋዘን አስተዳደርና አያያዝ፣ ጽዳት፣ ልየታና ደረጃ ማውጣት ያሉት ተግባራትን የሚያበረታታ፤<br>• የሁለተኛ ደረጃ የምግብ ምርቶችን ማቀነባበር፣ አስተማማኝ የማሽን አጠቃቀም እና ማሽኖችን በሙሉ አቅማቸው መጠቀም፣ ማስተካከል እና መጠገን የመሳሰሉትን፤<br>• የኢትዮጵያ ደረጃዎች መዳቢን የደረጃ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፣ ወይም ሌሎች አስፈላጊ የምስክር ወረቀቶችን በምግብ ነክ ምርቶች፣ በእንስሳት መኖ እና በሰራተኞች ጤንነት እና የአካባቢ ጥበቃ ረገድ ያሉ የምስክር ወረቀቶችን ለማግኘት የሚያስፈልጉ ወጭዎች፤<br>• በቢዝነስ አስተዳደር ዘርፍ የክትትልና ድጋፍ (coaching) አገልግሎት መስጠት፤<br>• እንደ ገበያ ጥናት፣ የአመራር ክህሎቶች ወዘተ ያሉ የአቅም ግንባታ ተግባራት፤<br>• የቢዝነስ ልማት ወጭዎችን (ቢበዛ የጠቅላላ በጀቱን 5 በመቶ)፤<br>• የመቀናጀ ፈንድ ለማገኘት የሚከፈል የባንክ ወለድን<br>• ለምርት ማሸጊያዎች እና ቀዝቃዛ ማቆያ ስልቶችን፤<br>• የምግብ ማሰራጫዎችንና ለመጠገንና እንደ አዲስ ለመስራት፤ |
| ከፍተኛው የፈንድ መጠን | 1,500,000 ብር (50,000 ዩሮ) |
| የሚፈቀድ ፈንድ መጠን | • ቢበዛ አንድ ደጋፍ ለአንድ አመልካች |
| | • ቢያንስ 50 በመቶ የፕሮጀክቱን ጠቅላላ ወጭ |

| | |
|---|---|
| ከአመልካች የሚጠበቀው መቀናጀ ፈንድ | • ሴት አመልካቾች እና ቢያንስ 50 በመቶ አባላቶቻቸው ሴት የሆኑ ቡድኖች/ የህብረት ስራ ማህበራት ከሚያቀርቡት የመቀናጀ ፈንድ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነውን በአይነት ማሳየት ይችላሉ፡፡ |
| የጊዜ ገደብ | • ከፍተኛው የፕሮጀክቱ የጊዜ ገደብ 24 ወራት ነው |
| የገንዘብ አለቃቅ ሁኔታ | • እንደ ፕሮጀክቱ ሁኔታ የቅድመ ፋይናንስ ክፍያ ሊከናወን ይችላል፤<br>• ድጋፍ ተቀባዩ ደንበኛ በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም የባንክ ሂሳብ መክፈት ወይም በስሙ አሊያም ግራንቱ በሚለቀቅበት ድርጅት ስም የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ማቅረብ አለበት፤<br>• የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ለድጋፍ ተቀባዩ የመጀመሪያውን ዙር ክፍያ ወደ ሂሳቡ ከማስተላለፉ በፊት ተቀባዩ መቀናጀ ፈንዱን በአማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ማስገባት ይኖርበታል፤<br>• የፕሮጀክት ድጋፍ ዩኒቱ የግል የንግድ ድርጅቶችን ቅድሚያ ክፍያውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን የሚችል በፕሮጀክቱ የቆይታ ጊዜ ሁሉ ጸንቶ የሚቆይ የባንክ ዋስትና እንዲያቀርቡ ሊጠይቅ ይችላል፤ |
| አመልካቹ ሊያሟላ የሚገባቸው መስፈርቶች | • የግራንት ውል ስምምነት በሚፈጽምበት ጊዜ አመልካቹ/ቾች ህጋዊ ምዝገባ ከሌለው በሚኖርበት ቀበሌ ከሚመለከተው ባለስልጣን የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤<br>• የታቀዱና ሊሰሩ የታሰቡት ፕሮጀክቶች ከአግሮ ቢግ ፕሮግራም አካባቢ በ100 ኪሎ ሜትር ሬድየስ ውስጥ ሊገኙ ይገባል፤<br>• በነጥብ አሰጣጡ ወይም በግምገማው ወቅት ሴት አመልካቾች እና በርካታ ሴት አባላቶች ያሏቸው የአርሶ አደር ቡድኖች እና የህብረት ስራ ማህበራት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፤ |
| የማመልከቻ አቀራረብ | ጉዳዩ የሚመለከታቸው አመልካቾች አግሮ ቢግ በይፋ የሚያወጣውን ማስታወቂያ ተከታትለው ፕሮፖዛሎቻቸውን በወረዳ ጽ/ቤቶች በኩል ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>• የፕሮግራም ድጋፍ ዩኒቱ በእያንዳንዱ የፕሮፖዛል ጥሪ ማስታወቂያ ላይ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጭብጦች እና ጽንሰ ሃሳቦች ይለያል፡፡<br>• የፈንድ ድጋፉ ሁለት ዙር የማመልከቻ ሂደት ያለው ሲሆን የመጀመሪያው የንድፈ ሀሳብ ኖት /Conpet note/ ሆኖ ይህ እንደጸደቀ ደግሞ ሙሉ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>• ኮንሰፕት ኖቶች እና ሙሉ ፕሮጀክቶቹ የፕሮጀክቱ አብዛኛው ተግባር በሚከናወንበት ወረዳ ጽ/ቤት ላይ ቀርበው ይታያሉ፡፡<br>• በወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ የተወከለ ሰራተኛ ተመድቦ የፕሮጀክት ፕሮፖዛሎቹ የሚጠቅሱትን ቦታ በአካል በማየት የተገኘው ውጤት የግምገማው አንዱ አካል እንዲሆን ይደረጋል፡፡<br>• በወረዳው የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ተገምግመው የተመረጡ ኮንሰፕት ኖቶች እና ሙሉ ፕሮፖዛሎች ከምክረ ሃሳብ ጭምር ለወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ ይላካሉ፡፡<br>• የወረዳው ስቲሪንግ ኮሚቴ በየሩብ አመቱ ወይንም ውጤት አሰጣጡ እንዳለቀ የሚገናኝ ሆኖ የቴክኒክ ኮሚቴው እንዲጸድቁ የላካቸውን ማመልከቻዎች እና ምክረ ሃሳቦች በመመርመር ፈንድ ሊፈቀድላቸው የሚችሉትን በመለየት የተመረጡ እና የጸደቁ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር ለፕሮጀክት ድጋፍ ዩኒቱ ይልካል።<br>• የፕሮጀክት ድጋፍ ዩኒቱ ያለው ገንዘብ በቂ መሆኑን እና ፕሮጀክቶቹ ተደጋጋሚነት አልምኖሩን በማጣራት የክልሉ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ እንዲያጸድቀው ለመጨረሻ ውሳኔ ይልላካል፡፡<br>የድጋፍ ገንዘብ ተቀባዮቹ በየወረዳቸው የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በመቅረብ የድጋፍ ውል ስምምነት ይፈርማሉ፡፡ |

| | |
|---|---|
| *ሪፖርት አደራረግ እና ክትትል* | የድጋፍ ተጠቃሚዎቹ በድጋፍ ውሉ ላይ በተቀመተው ቅጽ መሰረት ያላቸውን የስራ ሂደት ሁኔታ በየጊዜው ለወረዳው ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት እንዲሁም ለፕሮግራም ድጋፍ ዩኒቱ ይልካሉ፡፡ በመጨረሻም እያንዳንዱ ፕሮጀክት ፕሮጀክቶቹ ባሉበት ወረዳ ውስጥ በሚገኝ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ኦዲተሮች ኦዲት ይደረጋል፡፡ የየወረዳ ጽ/ቤት ሰራተኞች እንዲሁም የአግሮ ቢግ ሰራተኞች በየጊዜው የፕሮጀክቱን አፈጻጸም እና ተግባራት ይከታተላሉ፡፡ |